የወላጅ መምህራን ጉባኤ የልጅዎ መምህራንንና ሎሎችን ማለትም ልጅዎን በትምህርት የሚደግፋዋቸውን ለማግኘት እድል ከመስጠቱም ባሻገር ልጅዎ በተምህርት ቤት ውስጥ እንዴት እንደሚሰሩና ቤት ውስጥ ትምህርትን በተመለከተ እንዴት እንደሚታግዙዋቸው ለማወቅ እድል ይሠጣል፡፡

**ለስኬታማ የወላጅ መምህራን ጉባኤ ፍንጮች**

*በጉባኤው ውስጥ ልጅዎን ያሳትፉ፡-* ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን በወላጅ መምህራን ጉባኤ ያሳትፋሉ፡፡ ተማሪ መር የወላጅ መምህራን ጉባኤ ምንጊዜም ቢሆን ጠቃሚ ነው ምክንያቱም ለልጅዎ የሚሰጠው ጥቅም: 1) ስራዎቻቸውን ለመከለስ ያስችላል 2) ለቀጣይ የቀለም ትምህርት እድገታቸው ቀጣይ እርምጃዎችን በተመለከተ ሀሳብ ለመስጠት ያስችላል፡፡

**ከልጅዎ ጋር ይወያዩ፡-.** ልጅዎች ከመምህራቸው ጋር መወያየት ይፈልጉ እንደሆነ ይጠይቁዋቸው፡፡

**ጥያቄዎችን ያዘጋጁ፡-** ***እንደነዚህ አይነት ጥያቄዎችን ያዘጋጁ*** “ልጅዎቼ ትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ ምን ሰረተዋል” “ልጄ እንደ ክፍል ደረጃው እየሰራ ነውን” “ ልጅዎቼ ከፍል ውስጥ የተሰጣቸውን ስራዎች አጠናቅዋልን፡” “ልጄን ቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እችላለሁ” እናም “ በአመቱ ውስጥ ጥያቄዎችን መጠየቅ ብፈልግ ላገኘዎት የምችለው የላቀው አማራጭ ምንድን ነው?”

***ራስዎን ያግዙ፤*** በእንግሊዘኛ ቋንቋ ለመነጋገር ጥርጣሬ ካለዎት ትምህርት ቤቱን ወይም መምህራንን ቀድመው ካሳወቁ እርስዎን የሚያግዝዎት አስተርጓሚ ይረዳዎታል፡፡
ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብለው ይገኙ፡ ለእያንዳነዱ ጉባኤ ጊዜው አጭር ነው፡፡ሁሉም ቤተሰቦች መምህራንን መገናኘት መቻላቸውን ለማረጋገጥ ስብሰባ ጊዜ በፊት ቀደም ብለው መድረስ አለበዎት ጉባኤው በሰአቱ ባይጀመር እንኳን በትግስት ይጠባበቁ፡፡



**ከመምህራን ጋር አጋርነት መስርቱ፡ የልጆዎ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡** የልጅዎ መምህራን ለልጅዎ እድገትና ትምህርት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የእናንተ በአንድነት መስራት አስፈላጊ ነው፡፡

***ማስታወሻ መውሰድ፡-*** ማስታወሻ መውሰድ ጠቃሚ ነጥቦችን ለማስታወስ ይረዳል፤ በቤት ውስጥ ልጅዎችም ሆነ እርስዎ ቤት ውስጥ ምን መስራት እንደሚያስፈልግዎ ለማስታወሰ ይረዳዎታል፡፡

***ለጉባኤው ያለዎትን አድናቆት ይግለጹ፡-*** እርስዎ መምህሩ አንድ ቡድን መሆኑን አይዘንጉ፡፡ ልጅዎን በማስተማር ላይ እናንተ እያንዳንዳችሁ የምትጫወቱትን ሚና አወድሱ፡፡

**ከልጅዎ ጋር ውይይት ያካሂዱ፤** በጉባኤው ውስጥ የተንሸራሸረውን ሀሳብ ለልጅዎ ያካፍሉ፡፡ ልጅዎች ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ ማወቃቸውን ያረጋግጡ፡፡ለመምህሩ ቀሪ ጥያቄዎች እንዳላቸው ይወቁ፡፡ አሲፒኤስ የቤተሰብና ማህበረሰብ (ኤፍ ኤ ሲ ኢ) ትስስር ማዕከል እዚህ ያለው እነሱን ለመርዳት ነው!

**ከልጅዎ መምህርና ከትምህርት ቤቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ይኑሩዋችሁ፡-** ስለ ልጅዎ ለውጥ ከመምህሩ ጋር በየጊዜው በቅርበት ይወያዩ፡፡

# የወላጅና መምህራን ጉባኤ
## የወላጅ መሙያ ወረቀት

### ከጉባኤው በፊት:

***ከልጅዎ ጋር ውይይት አድርገዋል፤***

1. በትምህርት ቤት ውስጥ የሚመርጡት ትምህርት አይነትና ስራዎች ምንድን ናቸው? ______

2. ምን አይነት የትምህርት አይነቶችና ስራዎች ናቸው የማይወዱት፤ ለምን? ______

3. እኔ ከመምህሩ ጋር እንድወያይ የምትፈልጋቸው ጥያቄዎች ወይም ጉዳዮች አሉን? ______

***እንደ አስፈላጊነቱ በቅደም ተከተል ለመምህሩ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ይዘርዝሩ፤***

1. ______
2. ______
3. ______

### በጉባኤው ጊዜ፤

***በጥያቄዎች ላይ የመምህሩን መልሶች ያስቀምጡ፤***

1. ______
2. ______
3. ______

***ልጅዎ በትምህርት ቤት ያለውን ለውጥ በተመለከተ ማስታወሻ ይውሰዱ፤***

1.የስኬት ቦታዎች: ______

2. መሻሻል የሚገባቸው ቦታዎች: ______

***የስራ ዕቅድ አውጡ:***

1. መምህሩ የሚሰራው: ______
2. ወላጅ የሚሰራው: ______
3. ተማሪው የሚሰራው: ______